ስለ ፍትሃዊነት፣ ብዝሃነት እና አካታችነት (EDI) የዳሰሳ ጥናት የበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ፣ እባክዎን ድረ-ገጻችንንይጎብኙ።

የጤና እንክብካቤ ፍትሃዊነት ጽ/ቤት ዘረኝነትን የበለጠ የሚቃወም ድርጅት የመሆን ጉዞው ላይ ያጋጠመውን የእድገት ሂደት እና እንቅፋቶች የበለጠ ለመረዳት የፍትሃዊነት፣ ብዝሃነት እና አካታችነት የዳሰሳ ጥናት(EDI) እያካሄደ ነው። ስለ ዳሰሳ ጥናቱ የተለመዱ ጥያቄዎች ከዚህ በታች ተመልሰዋል።

## የፍትሃዊነት፣ ብዝሃነት እና አካታችነት የዳሰሳ ጥናት እንዲሞላ የምበረታታሁ ለምንድነው?

- ከሁሉም ሰው መስማት ይኖርብናል
- በበቂ ሁኔታ ያልተወከሉ እና የተገለሉ መሰረቶች ያሏቸው ግለሰቦች ይህን የዳሰሳ ጥናት ለማጠናቀቅ እንቅፋቶች ሊኖሩባቸው እንደሚችል እንገነዘባለን።
- የበለጠ ዘረኝነትን የሚቃወም ድርጅት ለመሆን በምንጥርበት ወቅት በመላው UW Medicine ውስጥ ያሉ አስተዳደራዊ፣ ክሊኒካዊ እና ትምህርታዊ ክፍሎችን ጨምሮ የOHCE ን ስራ እና የግለሰቦችን ቡድን ስራ ለመምራት የዚህ የዳሰሳ ጥናት ውጤቶች ጥቅም ላይ ይውላሉ።
- በEDI ላይ ለሚኖር የመሻሻያ ሂደት የእርስዎ ተሳትፎ አስፈላጊ ነው።
- ዘረኝነትን የበለጠ ለመቃወም ለሚሰራ ድርጅት ድምጾቻቸው ወሳኝ የሆኑ በባህል የተገለሉ ግለሰቦችን ብዙ ጊዜ መስማት ያቅተናል።
- ፍትሃዊነት በUW Medicine ውስጥ የስራችን ቁልፍ አካል ነው።
- ለመሻሻል አሁን ያለንበትን አካባቢ በደንብ መረዳት አለብን።

## ይህን የዳሰሳ ጥናት እንዲወስድ የተጋበዘው ማነው? የግዴታ ነው?

ሁሉም የUW medicine ሰራተኞች፣ መምህራንን እና ሰልጣኞችን ጨምሮ የዳሰሳ ጥናቱን እንዲያጠናቅቁ ተጋብዘዋል። ማንም ሰው የዳሰሳ ጥናቱን እንዲያጠናቅቅ አይጠየቅም እንዲሁም መልስ ላለመስጠት ከመረጡ በዳሰሳ ጥናቱ ውስጥ ማንኛውንም ጥያቄ መዝለል ይችላሉ።

## ይህ የዳሰሳ ጥናት መቼ ይጀመራል?

የዳሰሳ ጥናቱ ከጃንዋሪ 17 እስከ ፌብሩዋሪ 28, 2023 ኦንላይን ይካሄዳል።

## የዳሰሳ ጥናቱ ርዝመት እና ጊዜ

የዳሰሳ ጥናቱን ለማጠናቀቅ በአማካይ ከ15 ደቂቃ ያልበለጠ ጊዜ ይወስዳል። በአንድ ክፍለ ጊዜ ለመጨረስ ጊዜ ከሌለዎት የዳሰሳ ጥናቱን መጀመር እና ማቆም ይችላሉ። መመለስ የማይፈልጓቸውን ጥያቄዎች ለመዝለል መምረጥ ይችላሉ፡፡

## በEDI ጥናት ውስጥ ምን ተካቷል?

የዳሰሳ ጥናቱ በመላው UW Medicine ውስጥ የፍትሃዊነት፣ ብዝሃነት እና አካታችነት መለኪያዎችን መነሻ መስመር ለመለየት እና በድርጅት እና በመምሪያ ደረጃዎች ቅድሚያ የሚሰጣቸው የሚሰራባቸው ዘርፎችን ለመለየት የሚረዳ ለትግበራ የሚውል መረጃን ለማቅረብ ይሰራል። የዳሰሳ ጥናቱ የሚያተኩረው በUW Medicine ውስጥ የተለያዩ የግል ማንነቶች (እንደ ዘር፣ ጎሳ፣ ጾታ፣ አካል ጉዳተኝነት ወዘተ) የሰራተኛን ተሞክሮ እንዴት እንደሚቀርጹ ነው። ስለ ኢ-ፍትሃዊነት፣ አካታችነት፣ እና የአባልነት ስሜት ተሞክሮዎች የሚመለከቱ ጥያቄዎችን ያካትታል።

## ይህ የዳሰሳ ጥናት ለምንድን ነው የተዘጋጀው? እንዲሁም አሁን መደረጉ ለምን አስፈለገ?

UW Medicine የጤና እንክብካቤ ባለሞያዎቻችንን ደህንነት እና ሙያዊ እርካታ ለማሻሻል ቁርጠኛ ነው። ይህ አዲስ የዳሰሳ ጥናት በስርአቱ ውስጥ ባሉ ሁሉም አካላት የሚገኙ ሁሉንም የUW Medicine ሰራተኞችን በሚያሳትፍ ጠንካራ የማሻሻያ ዑደት ውስጥ የመጀመሪያው እርምጃ ነው። የእርስዎ ምላሾች አካባቢያችንን ለማሻሻል እና በስርዓት ደረጃ ማሻሻያዎችን ለመምራት በመረጃ ላይ የተመሰረቱ እርምጃዎችን እንድንወስድ ይረዱናል።

## የዳሰሳ ጥናቱ እንዴት ይከናወናል?

የዳሰሳ ጥናቱ የሚካሄደው በሶስተኛ ወገን RedCap፣ የኦንላይን የዳሰሳ ጥናት አስተዳደር፣ የመረጃ ቋት እና የሪፖርት ማድረጊያ መሳሪያ በመጠቀም ነው። የRedCap የዳሰሳ ጥናት መሳሪያ የኦንላይን ላይ የዳሰሳ ጥናቶችን ለማዘጋጀት እና ለማስኬድ የሚውል ክላውድ ላይ የተመሰረተ መሳሪያ ነው። የተጠናቀቁ የዳሰሳ ጥናቶች መረጃ በይለፍ ቃል የተጠበቀ ፣ቁጥጥር ባለው ተቋም የተዘጋ ቢሮ ውስጥ በሚቀመጥ እና ውስን ተደራሽነት ባለው የተመሰጠረ የኮምፒዩተር ሲስተም ውስጥ የማይክሮሶፍት አክሰስ ዳታቤዝ ግብዓቶችን በመጠቀም ይከማቻል። ከ EDI የዳሰሳ ጥናቱ ጋር የተገናኘ ማንነትዎን የሚለይ መረጃዎ ተደራሽ የሚሆነው የዳሰሳ ጥናቱ በሚሰጥበት ክፍለ-ጊዜ ብቻ መረጃውን እንዲያስተዳድሩ ለተሾሙ ውስን የ ITHS

ሰራተኞች ብቻ ነው። ይህ ክፍለ-ጊዜ ካለቀ በኋላ የዳሰሳ ጥናቱን በሚያጠናቅቁ ግለሰቦች እና ማንነትቶችን በሚለዩ መረጃዎች መካከል ያሉ ሁሉም ግንኙነቶች በሦስተኛ ወገን ታማኝ ወኪላችን ይደመሰሳሉ።

## ምላሾቼ በሚስጥር ይያዛሉ?

**አዎ፣ ሊለይ የሚችል የግል መረጃ በማንኛውም ምክንያት ለUW Medicine አይጋራም።** ለማንኛውም የፀደቀ ዓላማ የሚለቀቅ መረጃ የስነ-ሕዝብ፣ የመምሪያ ወይም የትምህርት ደረጃ ጥምረቶችን ጨምሮ ማንኛቸውም የግል መለያ መረጃዎቹ ተወግደው እና ከአስር በማያንስ ስብስብ ተደራጅቶ ይሆናል።

## የመረጃውን ሚስጥራዊነት እንዴት እንጠብቃለን?

የእርስዎን የግላዊነት ስጋቶች በቁም ነገር የምንመለከታቸው ሲሆን እውነተኛ ምላሽ ሲሰጡ ምቾት እየተሰማዎት እንዲሆን እንፈልጋለን። በጤና እንክብካቤ ፍትሃዊነት ጽ/ቤት እና በዳሰሳው ጥናት ምላሽ ጥሬ መረጃ መካከል መለያየትን ለመፍጠር፣ ጥናቱ የሚካሄደው በሦስተኛ ወገን ታማኝ ውክልና ስምምነት በ Institute for Translational Health Sciences ነው። የታማኝ ውክልና ስምምነቱ ITHS የተሳታፊ ማንነት መለያዎችን ሚስጥራዊነት እንደሚጠብቅ እና መረጃውን በየትኛውም ሁኔታ ለጤና እንክብካቤ ፍትሃዊነት ጽ/ቤት እንደማይሰጥ ይገልፃል።

በተጨማሪም፣ በግለሰብ ደረጃ ያለ መረጃ ለማንም አይጋራም። በድህረ-ገጹ ላይ ያሉ ሁሉም ሪፖርቶች እና መረጃዎች የዳሰሳ ጥናት ተሳታፊውን ግላዊነት እንዲጠብቁ ተደርገው ይቀናበራሉ። በተለይም፣ ውጤቶች የሚቀርቡት በማጠቃለያ (በድምር) መልክ ብቻ ነው ምክንያቱም ማንም በግለሰብ ግላዊ ባህሪያት ተለይቶ እንዳይታወቅ - የምናጋራው ውጤት 10 ወይም ከዚያ በላይ ምላሽ ሰጪዎች የሚይዙ ቡድኖችን ብቻ ነው። 10 ወይም ከዚያ ያነሱ ምላሽ ሰጪዎች ላላቸው ቡድኖች፣ ምላሾቹ ታግደው ይያዛሉ። በየትኛውም ጊዜ የዳሰሳ ጥናት ምላሾች በግለሰብ ደረጃ እንዲገኙ አይደረጉም።

## የዳሰሳ ጥናቱ እንዴት እንደሚወሰድ

የኢሜል ግብዣ ከዶክተር ቲም ዴሊት እና ፓውላ ሁስተን የኢሜል አድራሻ OHCE@uw.edu ን በመጠቀም ለሁሉም ብቁ ለሆኑ ግለሰቦች በጃንዋሪ 17፣ 2023 ወደ ኦንላይን የዳሰሳ ጥናቱ ከሚወስድ የግል ገጽ አገናኝ ጋር ይላካል። በድርጅቱ ውስጥ ያለ ሁሉም ሰው ለዳሰሳ ጥናቱ ልዩ የገጽ አገናኝ በUW ኢሜይሉ በኩል ይቀርብለታል። የዳሰሳ ጥናቱ እስከሚዘጋበት ፌብሩዋሪ 28፣ 2023 ድረስ ምላሽ ላልሰጡ ሰዎች ተመሳሳይ የኢሜይል የግል ገጽ አገናኝ የያዙ ወቅታዊ የኢሜይል አስታዋሾች ይላካሉ። የዳሰሳ ጥናቱ በአንድ ክፍለ ጊዜ ወይም በበርካታ ክፍለ ጊዜዎች ተመሳሳይ ገጽ አገናኝ በመጠቀም ሊጠናቀቅ ይችላል።

## በዚህ ድረ-ገጽ ላይ ያለውን መረጃ ለማግኘት የሚያስቸግር እክል አለብኝ። የዳሰሳ ጥናቱ ውጤቶች በተለየ ቅርፀት ተደራሽ ይሆናሉ?

UW Medicine አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ ለሁሉም ሰው ተደራሽ የሆነ የኦንላይን አካባቢን ለማቅረብ ቁርጠኛ ነው። ይህን ይዘት ሊጠቀሙ ካልቻሉ ወይም በዚህ ድረ-ገጽ ላይ ማንኛውንም መገልገያ መጠቀም ካልቻሉ፣ አማራጭ ቅርጸት ለማግኘት እባክዎን ወደ callieh@uw.edu ኢሜይል ያድርጉ።

## ይህን የዳሰሳ ጥናት ለማጠናቀቅ የሆነ ሰው ሊረዳኝ ይችላል?

አዎ።

## የዳሰሳ ጥናቱን በስማርት ስልኬ ወይም በሞባይሌ መውሰድ እችላለሁ?

አዎ።

## ጥያቄዎች እና ስጋቶችን በተመለከተ ማንን ማግኘት አለብኝ?

እባክዎን ለጥያቄዎች የፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ Callie Hunterን (callieh@uw.edu) ላይ ያግኙ። ኬሊየመጀመሪያ የግንኙነት ነጥብዎ ነች። እንዲሁም ማንኛውንም የግብረ ኃይል አባል ማግኘት ይችላሉ።